ሳምንታዊ ዜና ዘገባ
ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም.

- ከጅቡቲ ወደ መሀል አገር የሚወስደዉ መንገድ ለሁለት ቀናት ተዘጋ፣
- አራት ሹፌሮች ባታወቁ ታጣቂ ኃይሎች ተገደሉ፤
- ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ የሚመላለሱ ሹፌሮች የስራ ማቆም አድማ አደረጉ፣
- የነፃዉ ፕሬስ ጋዜጠኞች እንዳይሰሩ አዲስ ስዉር መመሪያ በበረከት ስምኦን ትዕዛዝ ወጣ ተባለ፣
- እዉቁ ድምፃዊ ቴወድሮስ ካሳሁን የእስራት ጊዜዉ መቀነሱ የፖለቲካ ዉሳኔ ነዉ ተባለ፣ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል ።

ዝርዝሩን እዚህ ላይ ተጭነዉ ያንብቡ <<>>

ከጅቡቲ ወደ መሀል ሀገር በሚወስደው  መንገድ ላይ በተለይ አዋሽ አርባ   ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ለሹፌሮች የእለት ተእለት ስጋት እየሆነ መምጣቱን የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እጅግ  እየከፋና እየሰፋ የመጣው አደጋ እየጨመረ በመምጣቱ የተነሳ ከ10 ዓመት በላይ በመስመሩ ሲያሽከረክሩ የነበሩ አሽከርካሪዎች ተስፋ እየቆረጡ ስራ እስከማቆም እየደረሱ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገለፆዋል::

በቅርቡ የካቲት 7 ቀን 2001 ዓ. ም. ከጠዋቱ 1 ሰዓት ላይ ወያኔ የአፋር ክልላዊ መንግስት ይዞታ ብሎ በሚጠራው ገዳማይቱ አካባቢ ሶስት ነባር የከባድ መኪና አሽከርካሪዎች የተገደሉ ሲሆን በዚያው ሰሞን ከአዋሽ ወደ ዱብቲ በሚወስደው መንገድ ላይም ጭፍራ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ሌላ አንድ የከባድ መኪና አሽከርካሪ ባልታወቁ ታጣቂ ኃይሎች መገደላቸው ታውቆዋል ::

እሁድ የካቲት 7 ቀን 2001 ዓ. ም. ሹፌሮቹ በመገደላቸው የተበሳጩት አሽከርካሪዎቹ  ከጠዋቱ 1 ሰዓት ጀምሮ ለሁለት ተከታታይ ቀናት ያለ ምግብ እና ውሀ ለ48 ሰዓታት ባሉበት ቆመው ያሳለፉ ሲሆን፤ ከዚህ በሁዋላ ለመስራት ዋስትና የሌለን በመሆኑ አንንቀሳቀስም በማለት አድማ መትተው እንደነበረም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ሶስቱ ሙዋች ሹፌሮች በጅቡቲ መስመር አንዱ ደግሞ በዱብቲ መስመር ባልታወቁ ታጣቂ ኃይሎች ከተገደሉ በሁዋላ አሽከርካሪዎቹ ተስፋ ቆርጠው ከመበሳጨታቸውም በላይ «በነፃነት ለመንቀሳቀስ  ዋስትና ስለሌለን ስራ አቁመናል» በማለት በበረሀ ውስጥ ለሁለት ተከታታይ ቀናት ባሉበት ገዳማይቱ አካባቢ መኪኖቻቸውን አቁመው የስራ ማቆም አድማ አድርገው የነበረ ሲሆን የፌዴራል ፖሊስ ወደ ስፍራው ሄዶ በግዳጅ አድማውን አቁመው ስራቸውን እንዲጀምሩ ሹፌሮቹን እንዳስገደዳቸው ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ከመስከረም 1 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በጅቡቲ መስመር ላይ እየደረሰ ያለው የታጣቂዎች እርምጃ እየሰፋና እየከፋ የመጣ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ እስከአሁን ድረስ ከ9 አሽከርካሪዎች በላይ እንደተገደሉና ገዳዮቻቸው አለመያዛቸውንም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

በእሩምታ ተኩስ ከፍተው የሹፌሮቹን ህይወት የቀጠፉት ታጣቂዎች ማንነት እስከ ትላንት ድረስ ያልታወቀ ሲሆን በጅቡቲ መስመር የሚመላለሱ ሹፌሮች በደረሰው ድንገተኛ ጥቃት በመደናገጥ አንዳንዶቹ ላልተወሰነ ጊዜ በሚል ስራቸውን ለማቆም እንደተገደዱም ታውቆዋል::

ሹፌሮቹ በተገደሉበት ወቅት ወደ ጅቡቲ የሚጉዋዙና ከጅቡቲ ወደ መሀል ሀገር የሚገቡ ከ3 ሺህ በላይ መኪኖች በመንገዱ ላይ ተደርድረው ለሁለት ቀናት ያለ ስራ

ያሳለፉ ሲሆን የመኪኖቹ ሹፌሮች እና ረዳቶቻቸው ለህልውናችን ዋስትና የለንም በማለት ያለ ምግብ እና ውሀ በበረሀ ውስጥ  የስራ ማቆም አድማ ያደረጉ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

እሁድ እለት ተገድሎ የተጣለው የሹፌሮቹ አስከሬን እስከ ማክሰኞ ዕለት ድረስ የሚያነሳው ጠፍቶ እንደነበር የገለፀው የደረሰን ዘገባ ከዚህ ቀደምም በተመሳሳይ ሁኔታ በታጣቂ ኃይሎች ግድያ የተፈፀመባቸው ሰዎች አስከሬን የሚያነሳው ጠፍቶ እንደሰነበተ አብራርቶዋል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት የሚደርስባቸውን የወያኔ  ጫና ተቋዋቁመው እየሰሩ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገሪቱ ስርዓት አልባ ክስተቶች እየታዩ በመሆኑ የሰው ልጅ እንደ እንሰሳ በየመንገዱ ተገድሎ እየተጣለ በመሆኑ ከፍተኛ ስጋት እና ጭንቀት ውስጥ የገቡት አሽከርካሪዎቹ በአንድነት ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሁኔታው ካልተስተካከለ ስራ ለማቆም እንደሚገደዱ እና ውሳኔው አሁኑ እንዲነገረን ሲሉ ደብዳቤ ማስገባታቸውን ይሄው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

ወያኔ የአሰብን ወደብ ለሻዕቢያ አሳልፎ ከሰጠና ሁለቱ ቡድኖች ግጭት ከፈጠሩ ወዲህ በጅቡቲ ወደብ መጠቀም የተጀመረ ሲሆን በተለይ በየጊዜው በሚደረገው የወደብ ታሪፍ እና የኮቲ ክፍያ እየጨመረ በመምጣቱ ሲያማርሩ የነበረው ሹፌሮቹ ወያኔ እራሱ ባመጣው እና በሰራው  ታሪካዊ ስህተት የተነሳ ለጅቡቲ ማጎብደድ ግድ ሆኖበታል ያለው የደረሰን ዘገባ በየጊዜው የሚጨምረውን የወደብ ታሪፍ ለማስቆም ለጅቡቲው ፕሬዝዳንት እጅ መንሻ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች መሬት በነፃ ቢያድልም ጂቡቲ ግን ከጭማሪው እንዳልተቆጠበች ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

ሰሞኑን ከተገደሉት አራት ሹፉሮች መሀከል የናዝሬት ከተማ ነዋሪ አቶ አስቻለው ከበደ የተባሉ የልጆች አባት የሚገኙበት ሲሆን፤የተቀሩትም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች መሆናቸውን ዘገባው ገልፆ ሹፌሮቹ ከተገደሉ ወዲህ  ከጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ የሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና እየተፈጠረ መሆኑንም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

አደጋው ከተከሰተ ከሁለት ቀናት በሁዋላ በሹፌሮች ጉትጎታ የመጡት የወያኔ የፌዴራል ፖሊሶች ሹፌሮቹን በግዳጅ መኪኖቻቸውን እንዲያነሱ እና ስራ እንዲጀምሩ ከማስገደዳቸውም በላይ አድማ አሳድማችሁዋል ያሉዋቸውን ሹፌሮች ለሰዓታት ከሌሎቹ ወደ ሁዋላ አሰቀርተው ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ እንደሰጡዋቸው ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

ከሚሌ ወደ ዱብቲ መስመር በሚወስደው መንገድ ላይ ጭፍራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢም  ባለፈው ሳምንት አንድ ሹፌር በተመሳሳይ መልኩ ባልታወቁ ታጣቂ ኃይሎች የተገደሉ ሲሆን በገዳማይቱም ሆነ በጭፍራ ስለተፈፀመው ግድያ

ኃላፊነት የወሰደ አካል ካለመኖሩም በላይ ወያኔም ማን እንደፈፀመው እስከአሁን ድረስ በግልፅ ያልተናገረ መሆኑ ታውቆዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጅቡቲ መንግስት በወደብ ታሪፍ ላይ ተከታታይ ሁለት ጊዜያት ጭማሪ በማድረጉ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች እያማረሩ ከመሆኑም በላይ በተለይ የውጭ ምንዛሪ በመቸገራቸው የተነሳ ለወደብ የሚከፍሉት እያጡ ያስጫኑት ዕቃ በዚያው እየተወረሰባቸው ለከፍተኛ ኪሳራ እየተዳረጉ እንደሚገኝም ዘገባው ገልፆዋል።

አብሪተኛው የወያኔ ቡድን ከዚህ ቀደም ገመናዬን ያጋልጡብኛል በሚል ከምርጫ 1997 ዓ. ም. ግርግር ጋር አሳብቦ ስራ እንዳይሰሩ ማዕቀብ የጣለባቸው የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች አሁን ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ እንዳይመለሱ አዲስ መመሪያ ማስተላለፉ ታወቀ።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው በተባለው በልቶ አደር የተሰባሰቡበት አዳራሽ ከፀደቀው አዲሱ የፕሬስ ህግ በተጨማሪ የወያኔው መሪ ቃል አቀባይ በረከት ስምዖን የመንግስት ኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት በአዲስ መልኩ እንዲዋቀር ተደርጎ በሚኒስትር መዕረግ ከተሾመ ወዲህ በህጉ ላይ ያልተጠቀሰና ያልወጣውን አዲስ መመሪያ አውጥቶ የነፃው ፕሬስ አባሎች ወደ ስራቸው እንዳይመለሱ ማድረጉን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።

ቀድሞ የነበረው ህግ ላይ ዋና አዘጋጅ የሚሆን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባለቤት መሆን እንደሚችል ያስቀመጠ ሲሆን አሁን ግን ዋና አዘጋጅ የሚሆን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባለቤት መሆን እንደማይችል መደንገጉንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

ህዝብ የማወቅ መብት አለው የሚለውን በመደፍጠጥ በመሳሪያ ኃይል ስልጣኑን የሙጥኝ ያለው የወያኔ ቡድን ቀጣይ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ በዓለም ላይ እጅግ አፋኝ እና ገዳቢ ህግ ከማውጣቱም በተጨማሪ ማንም ኢትዮጵያዊ ወደዚህ ሙያ እንዳይሰማራ ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑም ታውቆዋል።

ጋዜጠኞችን እያዋከበና እያንገላታ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በሁሉም መልኩ የህዝብን አንደበት ለጉሞ ለቀጣዩ ጊዜ ይረዳኛል በሚል አዲስ ህግ ከማውጣቱ በተጨማሪ ፍቃድ ለመውሰድ የሚፈልግ ሁሉ በረከት ስመኦን እና ተላላኪውን ሽመልስ ከማል ማስፈቀድ ግድ እንደሚል የገለጹት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በዚህም መሰረት ነባር የነፃው ፕሬስ አባሎች ፍቃድ እንዳይሰጣቸው የሚያደርጉበት ሌላ ስውር ዘዴ ማዘጋጀታቸውንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በተለይ ህዝቡ የሚደርስበትን በደል እና ግፍ እንዳይተነፍሱ እንዳያጋልጡ አፋኝ ህግ ያወጣው ወያኔ ማስታወቂያ ሚኒስቲርን አፍርሶ በመምሪያ ደረጃ ኮሚኒኬሽን በሚል

አዋቅሮ በረከት ስምኦንን በሚኒስትር ማዕረግ ሲሾመው ሽመልስ ከማልን ደግሞ ምክትል ሚኒስትር አድርጎ ማስቀመጡንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ከእስር ተፈትተው ወደ ስራ የገቡት ጥቂት ጋዜጠኞችም ቢሆን በተከታታይ በሚደርስባቸው የተለያዩ ጫናዎች ስራቸውን ለማቆም የተገደዱ ከመሆኑም በላይ አዳዲስ ክሶችን እያመጡባቸው ለእስር እየዳረጉዋቸው መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ቀድሞ ከቅንጅት አመራሮች ጋር እስር ቤት ገብተው የነበሩት ዳዊት ከበደና ወሰን ሰገድ ገ/ኪዳን አውራምባ ታይምስ እና ሐራምቤ በሚል ፍቃድ አውጥተው ስራ የጀመሩ ቢሆንም በየጊዜው በሚደረገው የወረቀት ዋጋ ጭማሪ እና ሌሎች ምክንያቶች ስራ ለማቆም መገደቸውን የገለፀው ዘገባ በተለይ ሐራምቤ ጋዜጣ ብዙም ሳትራመድ ልትቆም እንደቻለች ታውቆዋል፡፡

በቅርቡ ስራ ጀምረው እና በጫና እና በተለያዩ መንገዶች ስራቸውን ያቆሙ ጋዜጦች ሐራምቤ፤ ራዲ፤እንቢልታ፤እና ሌሎችም የሚገኙበት ሲሆን አዘጋጆቹም በተለያዩ ክሶች ተከስሰው ፍርድ ቤት እየተመላለሱ መሆኑም ታውቆዋል ፡፡ሰሞኑን ብቻ የሐራምቤው ጋዜጠኛ ውሰንሰገድ ገ/ኪዳን ፤የመሰናዘሪያው ጋዜጠኛ ወሰንሰገድ መርሻ፤የጎግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ውብሸት ታዬ ፤የአውራምባ ታይምስ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደ እና ሌሎችም በአንድ ጊዜ እያንዳንዳቸው ከስድስት ክሶች በላይ እየተከሰሱ ፍርድ ቤት እየተመላለሱ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በተቀነባበረና ሀሰተኛ የፈጠራ ክስ የታሰረው እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን ከተፈረደበት የስድስት ዓመት እስራት አራት አመቱ ተቀንሶ በሁለት ዓመት እንዲቀጣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ወሰነ፡፡

ከሚያዚያ 8 ቀን 2000 ዓ .ም. ጀምሮ በእስር ላይ ያለው እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን በከፍተኛ ፍርድ ቤት ለብዙ ወራት ሲከራከር ቆይቶ በሀሰተኛ ምስክሮች እና በተሰረዘና በተደለዘ የሰነድ ማስረጃ 6 ዓመት እስራት እና 18 ሺህ ብር ቅጣት የተወሰነበት ቢሆንም ውሳኔ ባገኘበት በ18ኛው ቀን ይግባኝ ጠይቆ ለጥር 18 ቀን 2001 ዓ. ም. ቀጠሮ ተይዞለት የቃል ክርክር ተደርጎ ለመጨረሻ ውሳኔ ለየካቲት 11 ቀን 2001 ዓ. ም.ተቀጥሮ የነበረ መሆኑ ይታወሳል፡፡

በዚህም መሰረት ጉዳዩን ሲመለከት የነበረው የብአዴኑ አባል የመሀል ዳኛ ዳኜ መላኩ ጉዳዩን መርምረን ውሳኔ እንሰጣለን ባለው መሰረት የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ. ም. ልዑል የወሰነበትን ስድስት ዓመት እና 18 ሺህ ብር ቅጣት በመቀነስ ሁለት ዓመት እና 11 ሺህ ብር እንዲቀጣ ወስኖዋል፡፡

እያወቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን በሀገር ውስጥ በሌለበት ዕለት የተፈጠረን አደጋ እንደ ፍርድ ቤት ቀጠሮ በይደር ይዘው በተቀነባበረና በተቀናጀ መልኩ ቲዲ ወደ

*ሀገር ቤት በሚመለስበት በማግስቱ እንደ አዲስ አደጋ እንደተፈጠረ አድርገው ክስ መስርተው ሲያስቃዩት እና ሲያንገላቱት ከቆዩ በሁዋላ የቅጣት ውሳኔ አሳልፈዋል፡፡*

*እውቁ ድምጻዊ ቲዲ አፍሮ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ላይ የተሰራበትን በደልና ግፍ በዝርዝር በ13 ነጥቦች ጨምቆ በጠበቃው አማካኝነት ተቃውሞ ያቀረበ ሲሆን በተለይም ሞተ የተባለው ወጣት በጥቅምት 22 ቀን 1999 ዓ.ም. መሆኑ እየታወቀ በካድሬዎቹ ትዕዛዝ ሰነዱ ተደልዞና ተሰርዞ በጥቅምት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. እንደተገጨና እንደሞተ ተደርጎ ከዳግማዊ ሚኒልክ ሆስፒታል ሰነድ የተባለው ማቅረቡና በተለይ ዳኛ ው ልዑል ገ/ማሪያም የተባለው አረመኔ ካድሬ የኩባው ሀኪም ለምስክርነት ቀርቦ እኔ እምነት የሌለኝ አህዛብ ነኝ ከማለቱም በተጨማሪ መስቀለኛ ጥያቄ እንዳይጠይቁት ከመከልከሉም በላይ ያቀረበው የምስክርነት ቃል በህክምና ሙያ ጉዳዩን የተመለከተው ሀኪም ብቻ ፅፎ ይሰጣል ሰነድም ተሰርዞና ተደልዞ አይቀርብም በማለት በግልጽ እና በማያሻማ መልኩ የገለፀ ቢሆንም የነቲዲ ጥያቄ ተቀባይነት አጥቶ የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥበት እንደቻለ ታውቆዋል፡፡*

*የጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሀል ዳኛ የወያኔ ካድሬ ዳኜ መላኩ ጥር 18 ቀን በዋለው ችሎት ለቲዲ ጠበቃ እና ለአቃቤ ህጉ ጥያቄዎችን ያቀረበ ሲሆን በዕለቱ ተከሳሽ ሲገጭ ተመልክቻለሁ ያለ ምስክር አለወይ? ብሎ ለዐቃቤ ህጉ ሲጠይቀው የለም በማለት ምላሽ የሰጠ ሲሆን በቲዲ የቀረቡ 13 ነጥቦች ያዘሉ አቤቱታንም መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት ለየካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. ቀጠሮ በሰጠው መሰረት የስድስት ዓመት እስራት እና የ18 ሺህ ብር ቅጣት የነበረውን አራት ዓመት እና 7 ሺህ ብር በማንሳት የሁለት ዓመት እስራት እና የ11 ሺህ ብር ቅጣት እንዲቀጣ መወሰኑ ታውቆዋል፡፡*

*ጉዳዩን ሲመረምር የቆየው የወያኔ ዳኛ ዳኜ መላኩ በቲዲ ላይ የቀረበው የተቀነባበረና ሀሰተኛ ክስ መሆኑን በግልፅ ያወቀ ቢሆንም የፓርቲውን ገመና ለመሸፈን ሲል ቅጣቱን ለማንሳት ሳይቻለው ቀርቶዋል፡፡*

*ውስጡን ሲያምሰው የቆየው ዳኛው ዳኜ መላኩ ድምፃዊ ቲዎድሮስ ካሳሁን እንደ ማንኛውም አደጋ አድራሽ ደረቅ ወንጀለኛ እንጂ ከፖለቲካ ጋር የሚያያዝ አይደለም ያለ ሲሆን በውጭ ግን ብዙ ብዙ እየሰማን ነው ፡፡ያ ግን የተሳሳተ ወሬ ነው ምንም ፖለቲካ ውሳኔ የለበትም በማለት ገልፆ የህዝቡን ጥርጣሬ በግላጭ አውጥቶታል፡፡*

*በማስከተልም ይግባኝ ብለህ ስትቀርብ ቅጣቱ በዛብኝ ብለህ ነበር እንጂ አልፈፀምኩም ማለት አልነበረብህም ያለው ዳኜ መላኩ ያም ሆኖ ግን እኛ አስተያየት አድርገን ቅጣቱን ቀንሰንልሀል በማለት ውሳኔ ያነበበ ሲሆን እውቁ ድምጻዊ ከውሳኔው*

**በሁዋላ አስተያየት አለኝ በማለት በተደጋጋሚ እጁን እያወጣ ቢጠይቅም እንድትናገር እድል አልሰጥህም በማለት ችሎቱ እንዲበተን አድርጎዋል፡፡**

**እውቁ ድምጻዊ ቲዎድሮስ ካሳሁን እጁ ከተያዘበት ዕለት ጀምሮ ሁለት ዓመት እስራት በማለት የተወሰነ ሲሆን አመክሮ ከታሰበለት አንድ ዓመት ከአራት ወር እንደሚታሰርና እንደሚፈታ የቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመው በዚህም መሰረት የወያኔ ካድሬዎች ሌላ ሰበብ ካልፈጠሩ በስተቀር ነሀሴ 8 ቀን 2001 ዓ.ም. የእስራት ጊዜውን ጨርሶ እንደሚለቀቅ ህጉ ያትታል ብለዋል፡፡**